የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ተምህርት ቢሮ

CITY GOVERNMENT OF ADDIS
ABABA EDUCATION BUREAU

ቁጥር ኢዳ/3579/ክ28-40/61
ቀን 24/02/2012

ለ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

<u>የውስጥ ኢንስፔክሽን ትግበራን ይመለከታል</u>

ተቋማት እስከ ህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ የውስጥ ኦዲት አድርገው እንዲጠብቁ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን ያሳወቅን በመሆኑ መልክቱ ለየተቋማቱ ተላልፎ በጥያቄው መሰረት እንዲፈጸም እየገለጽኩ የተላከልንን ደብደቤ አያይዘን ልክናል ፡፡

ከሰላምታ ጋር !

ደኛው ገብሩ ተስፋው
ምክትል ቢሮ ኃላፊ
Dagnaw Gebru Tesfaw
Deputy Bureau Head

ግልባጭ
ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት
ምክትል ቢሮ
ለተ/ሥ/ጥ/ማ/ም/ባለስልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

☎22-38-84 FAX 223888 ✉ 744 E-mail aa.cgeb@telecom.net.et

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣
ሙያ ብቃትና ምዘና
ማረጋገጫ ባለስልጣን፤

City Govenment of Addis Ababa
Education &Traning Quality
Professional Competence and
Assessment Assurance Authority

ቁጥር፡- ትሃ01/02/1293/12

ቀን ጥቅምት 18 2012

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

አዲስ አበባ

**ጉዳዩ፡- የውስጥ ኢንስፔክሽን ትግበራን ይመለከታል**

ከላይ በርዕስ ጉዳዩ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በ2011 ዓ.ም በተካሄደው የቢ.ፒ.አር. ጥናት መሰረት በቀድሞው በአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሪጉላቶሪ አጀንሲ አስተባባሪነት ተቋማት በራሳቸው የውስጥ ኢንስፔክሽን እንዲሰሩ ክትትል በማድረግ ይሰራ የነበረው ተግባር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህረት ቢሮ ስር በትምህርት ቤት ማሻሻል ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት እንዲመራ መደረጉ ይታወቃል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ለትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጠን በሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የተቋማትንና የባለሙያዎችን ብቃት የማረጋገጥ እንጂ የማብቃት ተግባሩን ለትምህርት ቢሮ የተሰጠ በመሆኑ በከተማ አስተዳደሩ ስር ያሉ የመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት ከወዲሁ በራሳቸው የውስጥ ኢንስፔክሽን እንዲያከናውኑ እና ለውጭ ኢንስፔክሽን ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ስለሆነም ተቋማችን የውጪ ኢንስፔክሽን ምዘና ከመሰራቱ በፊት በ2012 በጀት ዓመት መመዘን የሚገባቸውን ተቋማት በመለየት የውስጥ ኢንስፔክሽን ስራን እስከ ህዳር 15/2012 ዓ.ም ድረስ በማከናዎን ያሉበትን ጥንካሬና ክፍተት በመለየት ከወዲሁ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ በእናንተ በኩል ተገቢው ክትትል እንዲደረግበት እናሳስባለን ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ፍቅርተ አበራ
የትምህርትና ስልጠና ጥራት ዘርፍ
ም/ስራ አስኪያጅ

ግልባጭ

- ለባለስልጣኑ ዋና ስ/አስኪያጅ
- ለትምህርትን ስልጠና ዘርፍ ም/ሥ/አስኪያጅ
- ለት/ስ/ጥ/ማ/ም/ዳይሬክቶሬት
  አዲስ አበባ



ትሃ28-4013S
ከ02.2.2
10/2/2012